# የልማት ዕቅዱ የሶስት ዓመታት ውጤታማ ጉዞ

**አለማየሁ በቀለ 03/08/14**

አራተኛውን ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ ገዥው ፓርቲ ሰፊ የህዝብ ተቀባይነትን አግኝቶ ከተመረጠ በኋላ፤ ለህዝቡ ከገባቸው ቃሎች መካከል አንዱ፤ 'የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ግቦችን ለማሻሻል በላቀ ውጤት እንሰራለን' የሚል ነበር፡፡ በተለይም መላ የሀገሪቱ ህዝቦች በነቂስ በተሳተፉበት በዚህ ምርጫ፣ የስልጣኑ ሉዓላዊ ባለቤት የሆነው የሀገራችን ህዝብ ሃላፊነቱን ለኢህአዴግ ባሰረከበ ማግስት፤ ዕቅዱ ተክልሶና ለላቀ ውጤት ለመንቀሳቀስ በሚያስችል መልኩ በመንደርደሪያነት ተከልሶ ሊወጣ ችሏል፡፡

የኢፌዴሪ መንግስትም ይህን መነሻ በማድረግ አጠቃላይ ሀገራዊ ምርትን በአምስት ዓመታት ውስጥ በእጥፍ የማሳደግ ግብ በመጣል፣ እንቅስቃሴውን "ሀ" ብሎ ጀመረ—የዛሬ ሶስት ዓመት ተኩል ገደማ። የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ገቢ ለማሳደግም፤ ጥራት ያለው የትምህርትና የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋት እንዲሁም ዴሞክራሲ ስር እንዲሰድና መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ትልምንም ይዟል፡፡ ታዲያ ዕቅዱ በዚህ መልኩ በሁሉም መስኮች ለላቀ ውጤት ሊያበቃ በሚችል አኳኋን ከተከለሰና የልማቱ ዋነኛ ተዋናይ የሆነው ህዝብም በየደረጃው እንዲመክርበት ተደርጎ ጠቀሜታ ሃሳቦች ተወስደዋል—የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያውቁትና አስተያየታቸውም እንዲሰበሰብ በማድረግ ጭምር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ዕቅዱን መላው ህብረተሰብ እንዲያውቀው በተለያዩ መገናኛ እንዲገልጽ ተደርጓል፡፡ ምንጊዜም ለጋራ አጀንዳ እና ተጠቃሚነት 'ሆ!' ብሎ የሚነሳው የኢትዮጵያ ህዝብም ዕቅዱ ከተሳካ ሀገራችንን ወደ ላቀ የዕድገት ምዕራፍ እንደሚያሻጋግራት በማመን ለተፈጻሚነቱ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁነታቸውን በአንድ ድምጽ ነበር የገለጹት፡፡

ታዲያ ምንም እንኳን ህብረተሰቡ አንድ ሆኖ ለዕቅዱ ተፈጻሚነት ከጫፍ እስከጫፍ ቢነሳሳም፤ ሁሌም ከፀረ-ህዝብ ባህሪያቸው በመነሳት "የውሃ ቀጠነ" ተቃውሞን የሚያሰሙት ጽንፈኛ ፖለቲከኞች 'ዕቅዱ አይሳካም' ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ነገር ግን ህዝቡን ከጀርባው ያሰለፈው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት "ውሾቹ ይጮሃሉ፣ ግመሎቹ ግን ጉዟቸውን

ቀጥለዋል” እንዲሉ፣ የማይረባውን የተቃውሞ ጎራ አሪታን ወደ ጎን በመተው የተያዘው ግብ ከታለመለት ዓላማ እንዲደርስ ቀን ተሌት ሰርቷል፤ በመስራት ላይም ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው መንግስት የአምስት ዓመቱ የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ይሳካል ብሎ ሲነሳ፤ ከልማት ትልሙ በፊት የነበሩት ሰባት ዓመታት የሀገራችንን ኢኮኖሚ በእጥፍ ለማሳደግ በመቻላቸው ይህን ነባራዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ነበር፡፡ ዕቅዱን ከማስፈጸም አኳያ ወሳኙ ጉዳይና መተማመኛ ያደረገው የህዝቡን ሰፊ መነሳሳትና ርብርብ መኖሩን ከአረጋገጠ በኋላ ነበር–ወደ ትግበራው የገባው። እናም በዚህ ሁኔታ በከፍተኛ መነሳሳት የተጀመረው የልማት ርብርብ እነሆ ሦስት ዓመታትን አሳልፏል፡፡ በመሆኑም በዚህ ፅሑፌ የልማት ዕቅዱን ያለፉ ሶስት ዓመታት በውጤት የታጀበ ጉዞ መረጃዎችን በማጣቀስ ላስቃኛችሁ እሞክራለሁ።…

በቅርቡ የኢፌዴሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን የሦስት ዓመታት አፈጻጸም በመገምገም የተለያዩ ውሳኔዎችን ማሳለፉ ይታወቃል፡፡ ታዲያ ምክር ቤቱ በውሳኔው ዕቅዱ ባለፉት ሦስት ዓመታት በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በኢኮኖሚ ልማት፣ በመሰረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት እንዲሁም በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ላይ በማተኮር ግምገማውን አካሂዷል፡፡

በዚህም በ2005 የበጀት ዓመት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 9 ነጥብ 7 በመቶ ዕድገት የተመዘገበ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ግብርና የ7 ነጥብ 1 በመቶ፣ ኢንዱስትሪ 18 ነጥብ 5 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፍ የ9 ነጥብ 9 በመቶ ድርሻ እንደነበራቸው ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳን የተገኘው ዕድገት ከተቀመጠው ግብ አንጻር በመጠኑ ዝቅ ያለ ቢሆንም፤ ፈጣን፣ መሰረተ ሰፊና ከሰሃራ በታች ያሉ ሀገራት ካስመዘገቡት የ5 በመቶ አማካኝ ዕድገት ጋር ሲናጻጸር የላቀ ነው፡፡ ዕድገቱ በተለይም በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈታኝ ሁኔታዎች ተከስተው በነበረበት ወቅት የተገኘ እንደመሆኑ መጠን፤ መልካም የሚባል እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥን ለማምጣት በተደረገው ጥረትም፤ የግብርናው ዘርፍ በ2002 ከሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ከነበረባት የ46 ነጥብ 5 በመቶ ድርሻ በ2005 ወደ 42 ነጥብ 9 በመቶ ዝቅ ያለ ቢሆንም ቅሉ፤ ኢንዱስትሪ ከ10 ነጥብ 3 በመቶ ወደ 12

ነጥብ 4 በመቶ፣ የአገልግሎት ዘርፍ ደግሞ ከ44 ነጥብ 1 በመቶ ወደ 45 ነጥብ 2 በመቶ ከፍ ማለቱ ታውቋል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ግብርና የአምስት ዓመቱን ዕድገት የሚመራ፣ የሚያንቀሳቅስ ዋነኛ ሞተር እንደሆነና በእጥፍ የማሳደግ ግብ እንደተቀመጠለት ተደጋግሞ የተገለጸ ነው፡፡ ነገር ግን ግቡ በእጅጉ የተለጠጠ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ እናም በዋነኛነት የግብርናው ዘርፍ የአምስት ዓመቱን ዕድገት የሚመራና የሚያንቀሳቅስ ሞተር ነው ሲባል እነዚህን ጉዳዮች ታሳቢ ማድረጉን መገንዘብ ያሻል፡፡ በሀገራችን ከሚታረሰው መሬት ውስጥ ወሳኙን ድርሻ ይዞ እየሰራ ያለው አርሶ አደሩ ነው፡፡ በግብርና ልማት ላይ ከተሰማራው ጉልበት ውስጥ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆነው የተሰማራበት መስክ ይኸው ነው፡፡ ለግብርናም ከሚያስፈልጉት ግብዓቶች ወሳኞቹ ጉልበትና መሬት ሲሆኑ፤ በአሁኑ ወቅት መሬቱም ሆነ ጉልበቱ ከሞላ ጎደል በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ እየለማ ይገኛል፡፡ ካፒታሉን ስንመለከትም ቀላል የማይባል ድርሻን ይይዛል፡፡ እናም ህዝቡ በሰፊው በተሳተፈበትና የውጤቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ በሆነበት ሁኔታ ለውጥ መምጣቱ አይቀሬ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ከፍተኛ ግብ የተጣለበት የግብርና ምርት ለምን የተጠበቁበትን ግብ ማስመዝገብ አልቻለም የሚል ጥያቄ ማንሳት ግድ ይላል፡፡ እንደሚታወቀው በአንድ ሀገር ለሚዘገቡ ውጤታማ ክንውኖች አለም ዓቀፍ ገበያን እና የዋጋ ንረት እንዲሁም አጠቃላይ ሁኔታን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ግቡን ስንቃኘውም ውጤታማ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የአርሶ አደሩ ግብርና ልማት ጉዳይ በተለይም የአምስት ዓመታት ስራዎች ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ስራዎች መሆናቸውን ስንመለከት ደግሞ በ5 ዓመቱ ሊያመጣ ይገባል ተብሎ የተቀመጠለትን ግብ ለመምታት የሚያዳግተው ነገር ሊኖር አይችልም ተብሎ ይታመናል፡፡ ድህነትን ከመቀነስ አኳያም በ2003 ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከነበሩበት 29 ነጥብ 6 በመቶ በ2005 ወደ 26 በመቶ ዝቅ ማድረግ የተቻለ በመሆኑ፤ በ2007 ይደርስበታል ተብሎ የታቀደውን 22 ነጥብ 2 በመቶ ማሳካት እንደሚቻል ያረጋገጠ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም የመንግስትን ገቢ የመሰብሰብ አቅም ለማሳደግ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመያዝ ለሌሎች ዕቅዶች አጋዥ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የመንግስት የግብር ገቢን በድምሩ ወደ 17 በመቶ ለማድረስና ከዚሁ ውስጥ የፌዴራል መንግስትን ድርሻ ወደ 15 ለማድረስ ታቅዶ እየተሰራበት ነው፡፡

የ2005 የመንግስት ገቢ የመሰብሰብ አቅም የተመለከትን እንደሆነም የተመዘገበው የታክስ ገቢ ድርሻ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ 12 ነጥብ 5 በመቶ ብቻ በመሆኑ፤ አሁንም ከብዙ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ሊደረስበት ከታሰበው ግብ አንጻር ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ያም ሆኖ ግን የመንግስት ገቢን ከሞላ ጎደል በየዓመቱ በእጥፍ መጨመር በምንም መልኩ ቀላል ስራ ሊሆን አይችልም፡፡ አሁንም ይህን የመንግስትን የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ለማሳደግ የግብር አከፋፈል ላይ ያለውንና ባለሃብቶች ግብር ባለመክፈል የሚከብሩበትን መሰረታዊ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭን በማድረቅ በቀጣይ ሁለት ዓመታት የታያዘውን ግብ በላቀ ሁኔታ ማሳካት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በግብር አሰባሰብ ላይ ወጥ አሰራሮችን በመጠቀም የእያንዳንዱን ዜጋ ንብረትና ገቢ በውል እንዲታወቅ በማድረግ መስራት ያሻል፡፡

የመንግስት ገቢን ስንመለከት በተጓዳኝም ወጭንም በሌላ መልኩ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ በ2005 በጀት ዓመት ከጠቅላላው የመንግስት ወጭ ውስጥ 70 በመቶ ያህሉ ድህነትን በመቀነስ ረገድ ዓይነተኛ ሚና ላላቸው አምስት ዘርፎች /ማለትም ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለግብርና፣ ለውሃና ሳኒቴሽንና እንዲሁም ለገጠር መንገድ እንዲውል በመደረጉ የዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ እንደነበረው ተረጋግጧል፡፡

የአምስት ዓመቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት ከተያዙ ግቦች መካከል የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ማሳደግ አንዱ ነው፡፡ የቁጠባ አቅማችንን በማሻሻል በአምስት ዓመታት ውስጥ 15 በመቶ የሚደርስበት፣ ለቀጣዩም በተመሳሳይ ፍጥነት የሚያድግበት ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ ስትራቴጂያዊ መፍትሄ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ስትራቴጂያዊ መፍትሄ 'በ2005 ግቡ ስንት ደርሷል?' ማለት የግድ ይላል፡፡ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ምጣኔ በ2002 ከነበረበት 5 ነጥብ 2 በመቶ በ2005 ወደ 17 ነጥብ 7 በመቶ ሊያድግ ችሏል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ሊደረስበት ከተያዘው የ15 በመቶ ግብ ላይ የተመዘገበ አፈጻጸም መሆኑን በማረጋገጥ በ2007 ወደ 20 በመቶ ከፍ ለማድረግ ጥረት

መደረግ እንዳለበትም ተቀምጧል፡፡ ይህ የሚያሳየው የህብረተሰቡ የመቆጠብ አቅም እያደገ መምጣቱን እና ከዕቅድ በላይ መመዝገብ መቻሉን ነው፡፡

በሌላ በኩል ፈጣን ዕድገትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ማካሄድና የሚከናወነው ኢንቨስትመንትም ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ያለማቋረጥ በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድጉ ሀገሮች ከብሔራዊ ገቢያቸው ውስጥ ከ25 እስከ 30 በመቶ የሚሆነውን ለኢንቨስትመንት ያውሉታል፡፡

ከዚህ አኳያ በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድም ከብሔራዊ ገቢያችን ከ30 በመቶ የማያንሰውን የኢንቨስትመንት ወጭ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ በ2002 ከነበረበት 24 ነጥብ 7 በመቶ በ2003 ወደ 33 በመቶ ከፍ ብሏል። የወጭ ንግድ አፈጻጸምም በ2005 የ3 ነጥብ 1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ መመዝገቡንና ያለፉት ሦስት ዓመታት አማካኝ ዕድገቱ 16 ነጥብ 5 በመቶ ሊሆን ችሏል። ይህም ከዕቅዱ ግብ ጋር ሲነጻጸር ወደ ኋላ የቀረ በመሆኑ፣ በቀሪው ጊዜ አካክሶ መሄድ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

እንደሚታወቀው የኢንዱስትሪ ልማት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ውስጥ ተካትተው እየተሰራባቸው ካሉት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ውስጥ ወሳኝ ቦታ የተሰጠው ደግሞ ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው በቅድሚያ በከተሞች የስራ ዕድል የሚፈጥረው ዋናው ዘርፍ ስለሆነ እንዲሁም የኢኮኖሚ ልማት ዕቅዱ አንድ መሰረታዊ የስራ ዕድል መፍጠሪያ ማጠንጠኛ በመሆኑ ነው፡፡

አነስተኛ እና ጥቃቅን ተቋማት ዋነኛ የስራ ዕድል ፈጣሪ ሃይሎች የሚሆኑት እንደኛ ባሉ ሀገሮች ብቻ አይደለም። እንደ እነ አሜሪካ ባሉ ያደጉ ሀገራት ጭምርም የሚሰራባቸው ናቸው፡፡ እናም ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ለዘለቄታውም ዋናዎቹ የስራ ዕድል ምንጮች ስለሆኑ ነው— ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተከናወኑ ያሉት፡፡ በኢንዱስትሪና ማኑፋክቸሪንግ ልማት የላቀ ደረጃ ላይ የደረሰችውና እንደ እነ ትዮታና ሶኒ ያሉ ዓለም አቀፍ ግዙፍ ኩባንያዎችን ባለቤት የሆነችው ጃፓን እንኳን ሳትቀር፣ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው የልማት ስራዋን የምታከናውነው በማኑፋክቸሪንግ ተቋሞቿ ነው፡፡

እናም ተቋማቱ ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን የህዳሴው ጉዟችን ሲጠናቀቅም በኢንዱስትሪ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዋናዎቹ አምራች ሃይሎች መሆናቸው ስለማይቀር፣ ኢንዱስትሪን

በለተይም ማኑፋክቸሪንግን በከፍተኛ ፍጥነት ለማሳደግ የተቀየሰው የሀገራችን ዕቅድ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ልማትን ቅድሚያ መስጠቱ አይቀሬ ይመስለኛል፡፡

ስለሆነም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የልማታዊ ባለሃብት መፍለቂያ መሣሪያዎች በመሆናቸውም ጭምር በቅድሚያ ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪው ዘርፍ በተሰጠው ትኩረት አዳዲስ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲደራጁ የመደገፍና ነባሮችም እንዲጠናከሩ ብሎም ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ የማድረግ ስራዎች በስፋት ተከናውነዋል። በዚህም በ2005 ለ2 ሚሊዮን 21 ሺህ 670 ዜጎች ጊዜያዊና ቋሚ የስራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡

የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዋነኛ አንቀሳቃሽ የሆኑ ባለሃብቶችን የመደገፍ ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉን እንዲሁም የኢንዱስትሪ መንደር ግንባታዎችም በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ገቢራዊ እየሆኑ ነው። በመሆኑም ወደ ገበያው የገቡትና ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ መላክ የጀመሩ ኢንዱስትሪዎች ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት የበኩላቸውን ሚና እየተጫወቱ ነው። ይህም ስራ በየጊዜው ከባለሃብቶቹ ጋር በሚደረግ ምክክር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

እንደሚታወቀው በአምስት ዓመቱ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ሌላኛው ግብ የተጣለበት የመሰረተ ልማት ግንባታን የማስፋፋት ዘርፍ አንዱ ነው፡፡ በሶስት ዓመቱ ውስጥ ዘርፉን በ2002 አጠቃላይ በሀገሪቱ የነበረው 48 ሺህ 800 ኪሎ ሜትር መንገድ፣ በ2005 ወደ 58 ሺህ 338 ኪሎ ሜትር ማድረስ ተችሏል። በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽ ፕሮግራምም እስከ 2005 መጨረሻ ድረስ 27 ሺህ 628 ኪሎ ሜትር መንገድ መገንባቱን እንዲሁም የገጠርና የከተማ የመጠጥና ውሃ የቴሌኮም ማስፋፊያዎች እንዲሁም የባቡር መስመር ዝርጋታ እና ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ የሃይል ማመንጫ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት እየተከናወኑ ናቸው፡፡

በማህበራዊ ልማት መስክ የተደረገውን እንቅስቃሴን በተመለከተም፤ በ2002 በሀገሪቱ 26 ሺህ 951 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር በ2005 ወደ 34 ሺህ 495 ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ የተማሪዎች ቁጥርም በ2002 ከነበረበት 15 ነጥብ 8 ሚሊዮን በ2005 ወደ 17 ነጥብ 4 ሚሊዮን ማደጉ ተረጋግጧል፡፡ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው የትምህርት

ሥርዓቱ ያልተማከለ እንዲሆን በማድረጉ፤ የትምህርት ተደራሽነት በማስፋፋት ተገቢነቱን፣ ፍትሐዊነቱን እንዲሁም ጥራቱን በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ለውጦችን ማምጣት አስችሏል፡፡

ከዛሬ 20 ዓመት በፊት 20 በመቶ ገደማ የነበረው የአንደኛ ደረጃ ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ፤ በአሁኑ ወቅት ከ95 ነጥብ 1 በመቶ በላይ ደርሷል፡፡ የደረጃው ንጥር ተሳትፎም ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ከ6 እጥፍ በላይ መጨመሩን የመሰከሩ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ የሀገሪቱ የልማት አጋሮች ጭምርም ያረጋገጡትና ዓለም አቀፍ ዕውቅና የተቸረው ታላቅ ውጤት ነው፡፡

እርግጥም ይህን የትምህርት ተደራሽነት በከፍተኛ ደረጃ ለማስፋፋት የተቻለው፤ የትምህርት ቤቶች ግንባታ ያልተማከለ ስርዓትን በመከተሉ ብሎም ከሌሎች ትምህርት ቤቶች በራሳቸው በጀትና ተቋማዊ በሆኑ መልኩ ህዝቡ ባለቤት እንዲሆን በመደረጉና ሁለንተናዊ ድጋፍ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ ስለተከናወነ ነው፡፡ ይህም በሀገሪቱ በመቶ ዓመታት ውስጥ ያልተገነቡ ትምህርት ቤቶች ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ብቻ ተገንብተው ተማሪዎችን እንዲያስተናግዱ አድርጓል፡፡ የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተም፤ በ2002 ዓ.ም 1 ሺ.ህ 335 የነበሩ ትምህርት ቤቶች በ2005 ወደ 1 ሺ.ህ 912 የደረሰ ሲሆን፤ የተማሪዎች ብዛትም በ2005 ዓ.ም ወደ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ደርሷል፡፡

የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ያልተማከለ አካሄድን የሚከተል መሆኑ፤ ስርዓተ-ትምህርት በመቅረፅ ረገድ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ አስችሏል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ መሰረታዊ የሥርዓተ ትምህርት ሰነዶች (የስርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ አጥ.ጋቢ. የችሎታ መለኪያ) በየደረጃ ማስጠበቂያ መሣሪያነት በማዕከል ከተዘጋጀ በኋላ፤ የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፍት የሚዘጋጅበት በክልሎች የማስተማሪያ ቋንቋና የክልሎችን ተጨባጭ ሁኔታን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡  ይህም እስከ ዛሬ ድረስ በሀገሪቱ አንዱ የትምህርት ሥርዓቱ ችግር የሆነውን የስርዓተ ትምህርት ተገቢነትን ለመፍታት የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት አኳያም፤ የቅበላ መጠኑ እየጨመረ ባይመጣም ከኢንዱስትሪው ጋር በመተሳሰር ለወጣቶች የተግባር ትምህርት በመስጠት ስራው እየተሻሻለ መምጣቱ ተረጋግጧል፡፡ ያም ሆኖ ግን በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከ20 ዓመታት

በፊት 17 የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት የነበሩበት ሁኔታ ተለውጦ፤ ዛሬ ላይ የተቋማቱ ቁጥር ከ505 በላይ ደርሷል፡፡

በሌላ በኩልም የከፍተኛ ትምህርት ለሁሉም የቅድመ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች ተሳትፎ በግልና በመንግስት 553 ሺህ 848 የደረሰ ሲሆን፤ በአጠቃላይ በከፍተኛ ትምህርት ፕሮራም በዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ለማድረስ የታሰበውን ግብ አስቀድሞ ሊደረስበት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በከፍተኛ ትምህርት አቅርቦት እና ተደራሽነት ለማሳደግ በተከናወኑ ተግባራት የመንንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ 31 መድረሳቸው በቀጣይ 2 ዓመታት በዕቅድ ደረጃ ሊደረስበት ከታሰበው ዕቅድ አንጻር ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው በአምስት ዓመቱ የልመት ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል የጤናው ዘርፍ አንዱ ነው፡፡ ሁላችንም እንደምንገነዘበው አምራች ዜጋ የመፍጠር ጉዳይ፤ ጤነኛ ዜጋ ከመፍጠር ተነጥሎ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ስለሆነም የጤና እና የትምህርት ፕሮግራሞች ሁልጊዜም ቢሆን ተጣምረው መታየት ይኖርባቸዋል፡፡

የጤና ፕሮግራም ከሌሎች ፕሮግራሞች ለየት የሚያደርጉበት ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀሪያውና ዋነኛው ሰፊውን የገጠር ህዝብ ለማገልገል የተቃኘና በመሰረታዊ የጤና አገልግሎት ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡ የአምስት ዓመቱን ግቦች ለማሳካት በተለይም የህጻናትንና የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የቅድመና ድህረ ወሊድ አገልግሎት፣ የህጻናት ክትባት፣ የወባና የሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥር በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተሰርተዋል፤ በመሰራት ላይም ይገኛሉ፡፡ በተለይም የእናቶችንና የህፃናትን ሞት በመቀነስ ረገድ ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ያስደመመ ውጤትም ተገኝቶባቸዋል– ሀገራችን በመስኩ የምዕተ-ዓመቱን የልማት ግብ አስቀድማ አሳክታለችና። ታዲያ በዚህ ክንዋኔ ውስጥ የህብረተሰቡ ተሳትፎ በተለይም የሴቶች አደረጃጀቶች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

የጤና ተቋማት ግንባታን በተመለከተም፤ በ2002 ዓ.ም የጤና ጣቢያ ብዛት 2 ሺህ 142 የነበረ ሲሆን፤ በ2005 ዓ.ም ወደ 3 ሺህ 100 ያደገ በመሆኑ በዘርፉ የተቀመጠውን

ስታንዳርድ በአጭር ጊዜ ማሳካት የሚያስችል ተስፋ ሰጪ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ ለውጤቱ መገኘት መንግስት ለመሰረተ ጤና አገልግሎት ቅድሚያ ሰጥቶ የአገልግሎት ሽፋኑን ለመጨመር ያደረገው ርብርብ ትክክለኛና የህዝባዊ ባህሪው ዓይነተኛ ማረጋገጫ ነው፡፡ በቀሩት 2 ዓመታት ውስጥም በጤናው ዘርፍ የተያዘውን ግብ ለመምታት በአገልግሎት ሽፋን ረገድ ያሉትን ጉድለቶች ለማሟላትና ከሁሉም በላይ የአገልግሎት ጥራቱን ለማሻሻል ትኩረት መስጠቱ ትክክለኛና ተገቢ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር ስትራቴጂን በመተግበር ረገድም ውጤት ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ የተጀመሩ ተግባሮች አበረታች በመሆናቸው የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው በቀጣዮቹ ዓመታት ይበልጥ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ ከመልካም አስተዳደር አኳያ ዋናው ግብ እንከን የለሽ መንግስት መፍጠር ሳይሆን፣ ብዙ ትልልቅ ስህተቶችን የማይሰራና የተሰሩትን ፈጥኖ ተገንዝቦ የሚያስተካክል መንግስት ለመፍጠር እየተሰራ ነው። እርግጥ መንግስት የሰዎች እንጂ የመልዓክት ስብስብ ባለመሆኑ በዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር መስክ በየትኛውም ሀገር ፍፁማዊ የሆነ አሰራር ሊኖር አይችልም። በመሆኑም በሀገራችንም የተገነባው መንግስት ራሱን በራሱ እያረመ የሚሄድ እንጂ እንከን የለሽ ሊሆን አይችልም– ፈፃሚዎቹ ሰዎች ናቸውና። ያም ሆነ ይህ ግን ለመልካም አስተዳደሩም ሆነ ለዴሞክራሲ ባህል ግንባታው መሰረታዊው ጉዳይ፤ የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካ ኢኮኖሚን የበላይነት መናድ ወሳኝ በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን ጠጠር መወርወር ይኖርበታል፡፡

በልማት ዕቅዱ ሶስት ዓመታት ውጤታማ ጉዞ ውስጥ በሲቪል ሰርቪስ፣ በፍትህ አካላትና በሌሎችም የተጀመሩ የሪፎርም ስራዎች ተጠናክረው የቀጠሉ ሲሆን፤ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካን በማስወገድ ለልማታዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የበላይነት መረጋገጥ ያለሰለሰ ጥረት ተረርጓል። በዚህም የሴቶችንና የወጣቶችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ በ2005 የተጀመረውን የሴቶችን የውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎ በተለያየ ደረጃና ዘርፎች የማሳደግ ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በአጠቃላይ በ2005 በጀት ዓመት በሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት 9 ነጥብ 7 በመቶ ተመዝግቧል። ይሁንና የተገኘው ዕድገት ከተቀመጠው ግብ አንጻር በመጠኑ ዝቅ ያለ ቢሆንም፤ ፈጣን፣ መሰረተ ሰፊና ከሰሃራ በታች ያሉ ሀገራት ካስመዘገቡት የአምስት በመቶ

አማካኝ ዕድገት አንጻር ሲታይ የላቀ ነው። በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያ ፈታኝ ሁኔታዎች ተከስተው በነበሩበት ወቅት የተገኘ ዕድገት በመሆኑም መልካም የሚባል ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን የሀገራችን ጠቅላላ ዕድገት እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ ፈጣንና ተከታታይ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም።

ምንም እንኳን በ2005 የበጀት ዓመት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት የግብርናው ዘርፍ የ7 ነጥብ 1 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ከተጣለበት ግብ በመጠኑ ዝቅ ማለቱን ብንመለከትም፤ በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 202 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ምርት፣ በ2005 ዓ.ም ወደ 251 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ብሏል። ከዚህ በተጨማሪ ምርታማነቱ በአማካይ በ2002 ከነበረበት በሄክታር 15 ነጥብ 4 በኩንታል ወደ 17 ነጥብ 82 ኩንታል ማደጉ ለተሻለ ስራ የሚያነሳሳ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ የአምስት ዓመቱን የዕድገት እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አጠቃላይ የሶስት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ከተያዘው ዕቅድ ከፍ እና ዝቅ ያሉ ውጤቶች የተመዘገቡበት ቢሆንም፤ ዝቅ ያሉት በቀሪዎቹ ሁለት ዓመታት የሚጠበቅባቸውን ግብ ያስመዘግባሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከፍ ብለው የተመዘገቡ ውጤቶችም ከተያዘላቸው ግብ በላይ እያስመዘገቡ እንዲሄዱ ግብ ተጥሎባቸዋል፡፡ ለዚህም የሁሉም ህብረተሰብ ርብርብ እና ተሳትፎ እንዳለፉት የስኬት ጉዞዎች ሁሉ፤ በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት ውሰጥም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ምክንያቱም የልማት ዕቅዱን በማሳካት መካከለኛ ገቢ ወዳላቸው ሀገራት ተርታ የምንቀላቀልበት ብሎም ህዳሴያችንን የምናረጋግጥበት ብቸኛው መንገዳችን ስለሆነ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ዜጋ እንደተለመደው በተሰማራበት የስራ መስክ ሁሉ የሶስት ዓመቱን ውጤት እንደ ምርኩዝ በመጠቀም የበለጠ የልማት ማማ ላይ በመውጣት የነገ እርሱነቱን መደላድል መፍጠር ይኖርበታል።